በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ፡- 204829

ቀን፡-01/02/2014ዓ/ም

ዳኞች- ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች ፡- ፍቅር አብራክ የእናቶችና የሕፃናት ስፔሻላይዝድ የሕክምና ማዕከል -ወኪል ንጉስ አወቀ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ዶ/ር ልንገርህ ተፈራ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተምርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጠ፡፡

## ፍርድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነው፡፡ የክርክሩን አመጣጥ ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ግልባጭ እንደተረዳነው ተጠሪ የስር ከሳሽ፤ አመልካች ተከሳሽ ሆኖ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ አመልካች ከሕግ ውጭ የሥራ ውሌን ስላቋረጠ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈል እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች ባቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆናቸው ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ በሥራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 92429 አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በፍሬ ነገሩን ክሱን ለመስማት ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ባቀረበው ይግባኝ መሠረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራቀኙን አከራክሮ ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሳኔ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ይዘትም ተጠሪ የሥራ መሪ ሆነው እያለ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያው ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም የሚል ሲሆን የሰበር አጣሪ ችሎትም በዚሁ ነጥብ ላይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪን ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርቡ በማዘዙ ተጠሪ የሥራ መሪ አይደለሁም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ሲደረግ ዋናው ክርክር ሳይጠናቀቅ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ጉዳይ መሆን አለመሆኑን? በጭብጥነት በመያዝ መዝገቡን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው ተጠሪ ባቀረቡት የሥራ ክርክር ላይ አመልካች የሥራ መሪ ናቸው፣ ጉዳዩ በሥራ ክርክር ችሎትና በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ መሠረት ሊታይ አይገባም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ቢሆንም ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት መቃወሚያውን ባለመቀበል በፍሬ ነገሩ ጉዳዩን ለመስማት ትእዛዝ ሰጥቷል፤ ሥረ-ነገሩ ላይ ውሳኔ አልሰጠበትም፡፡ አመልካች ይግባኝ ያቀረበው መቃወሚያው ውደቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም በሚል ነው፡፡ ክርክሩን በፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ መሰረት መምራት እና መቆጣጠር የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሲሆን በተገቢው ሁኔታ ካልተመራ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ዓላማዎች የሆኑትን እንደ አንጻራዊ እውነትን የመፈለግ፣ ሥነ-ሥርዓታዊ ፍትህ፣ ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት የመሳሰሉትን ማሳካት ስለማይቻል የተከራካሪዎችን መብት ይነካል፡፡

በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320(3) መሰረት ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት የሚሰጥ ትዕዛዝ እና የጉዳዩ የመጨረሻ ውጤቱ ሲታወቅ አብሮ ይግባኝ ሊቀርብበት የሚችል ጉዳይ ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል ተመልክቷል፡፡ ድንጋጌው በክርክር ሂደት በሚሰጥ ትዕዛዝ ሁሉ ይግባኝ ከቀረበ የተከራካሪዎችን ወጪና ጊዜ የሚያባክን፣ የፍርድ ቤትን ጊዜ የሚወስድ ከመሆኑም በላይ በአንድ ጉዳይ ብዙ ፋይል እንዲኖር የሚያደርግና የሥራ ጫና የሚፈጥር እንዲሁም በይግባኝ ክርክር ምክያንት የሥር ክርክሩ ከታገደም ክርክርን ውጤታማ፣ ወጭና ጊዜ ቆጣቢ በሆነ አግባብ መምራት እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ ይሕን ለማስቀረት የተቀረጸ ነው፡፡ ጉዳዩ የመጨረሻ ዕልባት ሲያገኝ አብሮ ይግባኝ በማቅረብ ለተከራካሪዎች መብታቸውን ማስከበር የሚችሉበት ሥርዓት ስለሚፈጥር ይግባኝ የማቅረብ መብታቸው ላይ ገደብ እንዳደረገ የሚወሰድ አይደለም፡፡ አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውደቅ በመደረጉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ ፍርደ ቤት ዋናው ክርክር ከመጠናቀቁ በፊት ይግባኝ የሚባልበት አይደለም በማለት ይግባኙን ውደቅ ማድረግ ሲገባው የቀረበውን ክርክር ተቀብሎና አከራክሮ ውሳኔውን ማጽናቱ ክርክሩን በሥነ-ሥርዓት ሕጉ አግባብ የመምራትና የመቆጣጠር ኃላፊነቱን አለመወጣቱን የሚያሳይና መሠረታዊ የሆነ የክርክር አመራር ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

<u>ውሳኔ</u>

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 241335 የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ/ም የሠጠው ውሳኔ በፍብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2. አመልካች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ በመደረጉ ያቀረበው ከሥረ-ነገሩ ውሳኔ በፊት ይግባኝ ሊባልበት የሚችል ጉዳይ አይደለም በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ችሎት ለወጣ ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

- የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
- የሥር መዝገብ ይመለስ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሄ/መ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም